Paid Leave Oregon

# በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች ሽፋን

## በኦሬገን ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ለቤተሰቦቻችን፣ ለጤና እና ለደህንነት ተፅእኖ ለሚያደርጉ አንዳንድ ለህይወት ወሳኝ ጊዜያት እየተከፈለላቸው እረፍት እንዲወስዱ የሚያስችል አዲስ ፕሮግራም።

### ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን (Paid Leave Oregon) ተሸፍነዋል?

ከግል ሥራ ተቋራጮችን ጨምሮ ከግል ሥራ ገቢ የሚያገኙ ሰዎች ለሽፋን በመመዝገብ እና መዋጮ በመክፈል በሚከፈልበት የዕረፍት ጊዜ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ መምረጥ ይችላሉ። ካልተመዘገቡ አይሸፈኑም።

### የንግድ ድርጅት ባለቤት ከሆንኩ በግል ሥራ ተዳዳሪ ነኝ ወይም የግሌ ተቀጣሪ ነኝ?

ይህ እርስዎ ለራስዎ በሚከፍሉበት ሁኔታ ይወሰናል። እርስዎ በቀረጦችዎ የግል ተዳዳሪ ገቢ ሪፖርት የሚያደርጉበት ከድርጅቱ ትርፎችን የሚቀበሉ ከሆነ፣ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን (Paid Leave Oregon) የሚሸፈን ሠራተኛ ነዎት። በግብርዎ ላይ የራስዎ ተቀጣሪ ገቢ ብለው ሪፖርት ካደረጉት በ W2 ሪፖርት የሚያደርጉትን የከፍያ ቼክ የምያገኙ ከሆኑ፣ ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን መርሃ ግብር የሚሸፈኑ ተቀጣሪ ነዎት።

### ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን መሸፈን ከፈለግኩ፣ መቼ መመዝገብ እችላለሁ?

በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን ሽፋን እ ኤ አ ከጥር 1 ቀን 2023 ጀምሮ መመዝገብ ይችላሉ።

### ሽፋንን ለመምረጥ የሚያስፈልጉት ተፈላጊ ነገሮች ምንድን ናቸው?

በከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን ለመሸፈን፣ በግሉ ሥራ የሚተዳደር ሰው የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡-

- ባለፈው አመት ከግል ሥራ ቀረጥ የሚከፈል ቢያንስ $1,000 ገቢ ማግኘት
- የምርጫ ማስታወቂያ መሙላት
- በግል የሚተዳደሩበት ገቢያቸውን የሚያሳይ ግብር ያስገቡበትን ቅጂ ማቅረብ
- ለሦስት ዓመታት መዋጮ ለመክፈል መስማማት እና ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን በተጠየቀው መሰረት ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ

### በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች ለመዋጮ ምን ያህል መክፈል አለባቸው?

በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች በየሩብ ዓመቱ መዋጮ ይከፍላሉ። በግል ሥራ ለሚተዳደሩ የ2023 የመዋጮ ተመን 0.6% ከዓመታዊ ቀረጥ የሚከፈልበት ገቢ ሲሆን ከፍተኛው እስከ $132,900 ገቢ ነው። ለምሳሌ፣ አንድ ገቢ ሲኖረው፣
በግል ሥራ በዓመት 60,000 ዶላር ገቢ የሚያገኝ ሰው በሩብ አመት ከ90 ዶላር የሚበልጥ መዋጮ አይከፍልም።

## ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን በኩል የሚቀርቡት ጥቅማ ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

ሽፋን በዓመት 12 ሳምንታት የሚከፈልበት ፈቃድ እና ከእርግዝና ጋር በተያያዘ ተጨማሪ ሁለት ሳምንታት ይሰጣል። ብዙ ተቀጣሪዎች የደሞዛቸውን 100% ምትክ ያገኛሉ። የጥቅማጥቅምዎ መጠን ባለፈው አመት ባገኙ አማካይ አመታዊ ደሞዝዎችዎ ላይ ነው የተመሰረተው። በአሁኑ ጊዜ ዝቅተኛው ሳምንታዊ ጥቅማጥቅም በግምት $61 ይሆናል፣ እና ከፍተኛው ሳምንታዊ ጥቅማጥቅም በግምት $1,469 ይሆናል።

## በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች ጥቅማጥቅሞች ከተቀጣሪዎች ጥቅማጥቅሞች ጋር አንድ ናቸው?

አዎ። ስለ ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን ጥቅማጥቅሞች ተጨማሪ መረጃ በእንቴርኔት ላይ ነው።

**ጥቅማ ጥቅሞች መቼ ይጀምራሉ?** ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን በመስከረም 2023 ይጀምራል።

## አንድ በግል ሥራ የሚተዳደር ሰው ወዲያውኑ ጥቅማ ጥቅሞችን ማግኘት ይችላል?

ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን የተመዘገቡ የግል ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ለአንድ ዓመት መዋጮ ከከፈሉ በኋላ ሙሉ የጥቅማጥቅማቸውን መጠን ለማግኘት ብቁ ናቸው። ከአንድ አመት በታች መዋጮ እየከፈሉ ከሆነ የተቀነሰ
የጥቅማጥቅም መጠን ይቀበላሉ። በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች፣ አንድ ሰው ለአንዳንድ ጥቅማጥቅሞች ብቁ ለመሆን ቢያንስ ለአንድ ሩብ ጊዜ ሽፋን ሊኖረው ይገባል። ለምሳሌ፣ በመስከረም 2023 ከፊል ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ ለመሆን በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች እስከ ሰኔ 2023 መጨረሻ ድረስ መመዝገብ እና መዋጮዎችን በተመዘገቡበት ጊዜ እስከ ሰኔ 30፣ 2023 ባለው ጊዜ ውስጥ ባለው ገቢ ቢያንስ 1,000 ዶላር መክፈል አለባቸው።

## ለሽፋን የተመዘገቡ በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

በግል ሥራ የሚተዳደሩ ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን የተመዘገቡ ሰዎች ማድረግ ያለባቸው፣

- $ በየሩብ ዓመቱ መዋጮ መክፈል፣
- $ ገቢያቸውን ማሳወቅና እና ግብር ያስገቡበትን መግለጫ ቅጂ በየአመቱ እስከ ሚያዚያ 30 ድረስ ማቅረብ፣

## የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ ሽፋን ቁርጠኝነት ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል?

ከክፍያ ጋር ፈቃድ የሚሰጥበት ኦሬገን የተመዘገቡ በግል ሥራ የሚሠራ ሰው ከሦስት ዓመታትና ከዚያ በላይ መዋጮ ለመክፈል መስማማት አለበት።

## የተመረጠ ሽፋን (elective coverage) ሊሰረዝ ይችላል?

በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ውስጥ፣ በግል ሥራ የሚተዳደር ሰው ከአሁን በኋላ በግል ሥራ ካልሠራ ወይም ለኪሳራ ካመለከተ የሚከፈልበትን ፈቃድ መሰረዝ ይችላል። ከሶስት አመት ሽፋን በኋላ፣ በማንኛውም ጊዜ ሽፋንን መሰረዝ ይችላሉ።

**በግል ሥራ የሚተዳደርና እና ለቀጣሪ የሚሰራ ሰው አሁንም ለሽፋን መመዝገብ ይችላል?** አዎ በግል ሥራ ለሚተዳደሩ ገቢያቸው፣ ግለሰቡ መዋጮውን ራሱ ይከፍላል ። ለመደበኛ ሥራቸው አሰሪያቸው የሚያዋጡትን ክፍያ ከደመወዛቸው ላይ ይቀንሳል። ከዚያ፣ ፈቃድ በክፍያ ለመውሰድ ከፈለጉ፣ የጥቅማጥቅማቸው መጠን በሁለቱም በግል በሚሰሩት ገቢ እና ደሞዝ ላይ የተመሰረተ ይሆናል።